4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681

No_______________
Date 30/5/1999

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፤

በኢትዮጵያ፣ በሰሜን አሜሪካ፣ በአፍሪካና በመላው አውሮፓ ለምትኖሩ ኢትዮጵያውን በሙሉ፡፡

**ጥር ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. አዲስ አበባ ላይ ለተላለፈው የሐሰት የውግዘት ቃል ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የተላለፈ ውግዘትና መግለጫ፡፡**

በረዥሙ የክርስትና ጉዞ ቤተ ክርስቲያንን ክፉኛ የጎዳትና ለክፍፍልም የዳረጋት ከአሕዛብ በኩል የተመዘዘባት ሰይፍ ወይም ከውስጧ የተነሱ የመናፍቃን ሁከት አልነበረም፡፡ ከውጭ በአሕዛብ በኩል የተቀጣጠለውን የጥላቻ እሳት በውስጥ በክርስቲያኖች መካከል የነበረው ጽኑ ፍቅር ገድቦ አስቀርቶታል፡፡ እንዲሁም ከውስጥ መንጭቶ የክርስትናን ቀጥተኛ ጉዞ ያደነቃቅፍ የነበረውን የመናፍቃን ሴራ የቤተ ክርስቲያን ጠበቃዎች የሚባሉ አፖሎጂስትስ በወርቃማ ተጋድሏቸው፣ በጽሑፋቸውና በትምህርታቸው ተቋቁመውታል፡፡ በዚህ ዘመን ስለ ቤተ ክርስቲያን ቀጥተኛ ትምህርት በአንደበታቸው እየመሰከሩ ያመኑበትንና ከአባቶቻቸው የተረከቡትን እውነት በጽሑፍ እያሰፈሩ በሰማዕትነት ያለፉ አባቶች ብዙ ናቸው፡፡

ከእነዚህ ሁሉ ችግሮች በላይ የክርስትና ሃይማኖት ለመጀመሪያ ጊዜ በሁለት ጎራ እንዲከፈል ምክንያት የሆነው ጉዳይ የፖለቲካ ኃይሎች በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ ጣልቃ መግባት ነው፡፡ ለዚህም በ451 ዓ.ም የተካሄደውን የኬልቄዶንን ጉባኤ መጥቀስ ብቻ በቂ ማስረጃ ይሆናል፡፡ ይህ በዘመናችን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም በግልጽ የተፈጸመ እውነት ነው፡፡ ሐዋርያዊትና ታሪካዊት የሆነቻው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በታሪኳ እንደዚህ ዓይነት ምስቅልቅል ገጥሟት አያውቅም፡፡ በአለንበት ዘመን የቤተ ክርስቲያኒቱን ችግር ውስብስብ ያደረገው ጥላቻና የጎሳ ፖለቲካ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቦታ አግኝቶ በመስፋፋቱ ነው፡፡ ይህንን ሐቅ በማስረጃ ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ነጥቦች እናያለን፡፡

**ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የተሰደዱበት ምሥጢርና ያስከተለው ውጤት፤**

ስለ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬስ ስደት ሲነገር መሠረታዊ የሆነው ወሳኝ ነጥብ "ይህች ሹመት በአንድ ዘመን በአንድ ሀገር ለሁለት ሰዎች ልትሆን አይገባም፤ ይህ በአንድ ሀገር ከተደረገ ግን አስቀድሞ ለተሾመው ትጽና፡፡ ስለታመመ ፓትርያርክ ግን አእምሮውን ያጣ እንኳን ቢሆን ይድናል ብለው ተስፋ የሚያደርጉ ከሆነ ይጠብቁት…ከሹመት መሻር ግን ፍጹም ጉድለት ይገኝበታል" የሚለው በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ 4 ቁጥር 70-78 የተጠቀሰው ነጥብ ነው፡፡ ቅዱስ ፓትርያርኩ ከመንበራቸው የወረዱት ዓለም ዓቀፍ የሆነው የቤተ ክርስቲያን ቀኖና ተጥሶ እንደሆነ የተረጋገጠ ቢሆንም፣ ከሁሉም በላይ ግን የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ዕጣ ሳይደርስባቸው ተጠንስሶባቸው ከነበረው የሞት ሴራ በተአምር ተርፈው ለዚህ መድረሳቸው በራሱ አስገራሚ ታሪክ ነው፡፡

የወያኔ ኢሕአዲግ መንግሥት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን ከመንበራቸው ያወረደው ዓለማቀፉን የቤተ ክርስቲያን ቀኖና አፍርሶ መሆኑን ስለሚያውቅና በሕይወት መኖራቸው በራሱ ውሎ አድሮ ችግርን እንደሚያስከትል ስለሚገነዘብ ቅዱስነታቸው ጥበቃ በሌለበትና ለአደጋ በተጋለጠ ቦታ ወደ እንጦጦ ገዳም እንዲሄዱ የተገደዱበት ዋና ምክንያት በአልባሌ ሰው እንዲገደሉ ለማድረግ ታስቦ እንደነበር በመረጃ ተረጋግጧል። ይህ አልሳካ በማለቱ በእስር ቤት ማቅቀው ሕይታቸው እንዳለፈው እንደ ፕሮፌሰር አስራትና ዛሬም በአደጋ ላይ እንዳሉት ምርጥ የኢትዮጵያ ልጆች ቅዱስነታቸውን የሐሰት የክስ ሰነድ አዘጋጅቶ ለፍርድ የሚያቀርብ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ እንደነበር በወቅቱ ለቅዱስነታቸው የሚቀርቡ ግለሰቦች ምስጢሩን በማውጣት አስጠንቅቀዋቸዋል። በዚህም ምክንያት "በአንዷቱ ከተማ መከራ ቢያሳዩአችሁ ወደ ሌላይቱ ሽሹ" (ማቴ 10፡ 23) በተባለው አምላካዊ ቃል መሠረት ሕይወታቸውን ለማትረፍ ሲሉ ወደ ኬንያ ለመሰደድ ተገደዋል። ወደ ኬንያ መሄዳቸው የወያኔን መንግሥት ክፉኛ ስላበሳጨው ኬንያ በነበሩበትም ጊዜ ያሉበት ቦታ ተጠንቶ አደጋ እንዲጣልባቸው ብዙ ሙከራ ተደርጎ እንደነበር የታወቀ ነው። ነገር ግን የእግዚብሔር መለኮታዊ ጥበቃ ስላልተለያቸው ይኸውና እስከአሁን ድረስ በሕይወት ቆይተው ታላቅ ሥራ እየሠሩ ይገኛሉ።

በሃይማኖት ምክንያት መከራ ሲመጣ ወይም እንደ አሁኑ ከአንተ እኔ እበልጣለሁ የሚል ተፎካካሪ ሲነሳ ከሀገር ወጥቶ በስደት ሕይወትን መግፋት ለቤተ ክርስቲያን አባቶች አዲስ ነገር አይደለም። ታላቁ የቤተ ክርስቲያን ሊቀ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጥፋት ሳይኖርበት ከመንበሩ ተፈናቅሎ በስደት ብዙ ዘመን አሳልፏል። ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ አትናቴዎስም እንደ አባ ጳውሎስ ያለ መናፍቅ ጳጳስ በባለሥልጣናት ትዕዛዝ በወታደራዊ ኃይል ታጅቦ መንበሩን በነጠቀው ጊዜ በተደጋጋሚ 5 ጊዜ ከመንበሩ ተፈናቅሏል፤ ለ15 ዓመታት ያህልም በስደት ኑሯል።

ሐቁ ይህ ሆኖ ሳለ ግን የቅዱስ ፓትርያርኩን ስደት የሀገር ክዳት ወይም በሕመም አሳበው የተጣለባቸውን ኃላፊነት ላለመወጣት የፈጠሩት ችግር ለማስመሰል አንድ ጊዜ "መንጋውን ከዱ" ሌላ ጊዜ ደግሞ "በራሳቸው ፈቃድ ለቀቁ" የሚሉ የፈጠራ ቃላት ተደጋግመው ሲነገሩ እንሰማለን። መንጋውን ከዱ የሚለው ቃል የሚመለከተው በሀገር ውስጥ በድሎት ያሉትንና ኃላፊነታቸውን ያልተወጡትን ጳጳሳት ብቻ ነው። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ግን የተጣለባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ምንም ዓይነት ችግርና ሕመም የሌለባቸው መሆኑን በወቅቱ በጽሑፍ አረጋግጠዋል። ደግሞስ ከመንበራቸው በራሳቸው ፈቃድ ወረዱ ከተባለ ይህ ታላቅ የሀገርና የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ በመገናኛ ብዙኃን በራዲዮና በቴሌቪዥን አለመነገሩ ብዙ ደቂቃ ይፈጃል ተብሎ ይሆን! ወይስ ፈርመው የለቀቁበት ደብዳቤ አለመገኘቱ ምሥጢሩ ምን ሊሆን ይችላል!። እውነቱ ግን ከዚህ ቀጥሎ የተገለጸው ነው። ዛሬም ድረስ በሕይወት ያሉ እንደሚመሰክሩት 19 ጳጳሳት በጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ለዓይኔ ቢሮ ተጠርተው እኒህን ፓትርያርክ ካላወረዳችሁ መንግሥት ከእናንተ ጋር አይሠራም ተብሎ እንደተነገራቸውና ቀጥሎም የቤተ ክህነቱ በጀት እንደታገደ ማንም የማይክደው የአደባባይ ምሥጢር ነው። እንግዲህ ቅዱስ ፓትርያርኩ ከመንበራቸው የወረዱት በመንግሥት ኃይል ተገደው እንጅ ወደው እንዳልሆነ ከላይ የጠቀስናቸው ማስረጃዎች ማረጋገጫ ናቸው።

በአጠቃላይ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ መሰደድ ሁለት ገጽታ አለው። በአንድ በኩል የአባቶችን ስደት ተከትሎ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በውጪ ዓለም የተስፋፋችበትን ከመከራ የተገኘ መልካም አጋጣሚ ያየን ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ የራሷን መሪ ያሳደደችበትና በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ጥላቻ የተስፋፋበት መጥፎ አጋጣሚ መከሰቱን እናስተውላለን። ስደት ለአሳዳጁ መርገም ሲሆን ለተሳዳጁ ግን በረከት ነው። ዛሬ በሰሜን

አሜሪካ ያለችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአስገራሚ መልኩ አብባ፣ አድጋና ተስፋፍታ ስንመለከት እግዚአብሔር የእነዚህን አባቶች ስደት ምን ያህል እንደባረከው በዚህ እናረጋግጣለን።

**የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውን!!**

በተደጋጋሚ እንደተነገረው ብፁዕ ቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የተሰደዱበት መሠረታዊ ጉዳይ ከዚህ በላይ የተመለከተው ነው። በአሁኑ ወቅት አራት ኪሎ ላይ የሚሰማው ጩኸት ግን ይህን ሊያስተባብል የሚችል አይደለም። እነዚህ ከንቱ የሆኑና አእምሯቸው የተወሰደባቸው ሕገ-ወጦች ቃላት ሳይመርጡ የሚያስተላልፉት መግለጫ አዳማጭ እንደማይኖረው የታወቀ ቢሆንም የራስን ገመና ሳይሸፍኑ እንከን እንደሌለበት የቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ አካል እንደዚህ ልብን ሞልቶ ምዕመናንን ለማደናገር መሞከር በጣም የሚያሳፍር ነው። ይህ የራስን ጥፋት በሌላው ላይ ለማሳየት መሞከር ከወያኔ የተቀዳ ያረጀ ፖለቲካ ነው። ሎስ አንጀለስ ላይ በኦርጋን ሲዘምሩ የነበሩት አባ ጳውሎስ አሁን በጠብ ጊዜ ስለ ኦርጋን፣ ስለ ቅዳሴ ማርያምና ስለ ታቦት እያነሱ አባቶችን መናፍቃን የሚሉት ታዲያ ከመናፍቃን ጋር ሲታረቁ ኖሮ ነው እንዴ አሜሪካ ድረስ ሽማግሌ የሰደዱት? ደግሞስ እነዚህ አባቶች በየትኛው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ቀርበው ተጠይቀው ነው መናፍቅነታቸው የተረጋገጠው? ለሽማግሌዎች እሽ ብላችሁ የእኛን ሥልጣን ካከበራችው የቤተ ክርስቲያን አባቶች ናችሁ፣ አለበለዚያ ግን ስም እንሰጣችኋለን ይመስላል አዝማሚያው!! ግለሰቦቹ አንድም የተጻፈውን አንብቦ ማስተዋል ስለተሳናቸው ወይም ለበደለኛው ለአባ ጳውሎስ ስለወገኑ ነው እንጅ "የድንግል ማርያም ክብርና የነገረ ማርያም ትምህርት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባሕል" በተሰኘ ለመመሪቂያ በጻፉት መጽሐፋቸው በገጽ 147 ላይ ድንግል ማርያም የውርስ ኃጢአት እንዳለባትና ያለ ውርስ ኃጢአት እንዳልተወለደች የጻፉ አባ ጳውሎስ አልነበሩም!!። ሰይጣን ክርስቶስን፣ "ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ" (ማቴ 4፡10) ሲል ለማታለል እንደሞከረው አባ ጳውሎስ መልዕክተኛ ወደ ሰሜን አሜሪካ የላኩት ተጸጽተውና ከልባቸው ዕርቅ ፈልገው አልነበረም፤ ለክብራቸውና ለሥልጣናቸው ክፉኛ ተጨንቀው ነው እንጅ።

ደግሞስ አባ ጳውሎስና ጭፍሮቻቸው ትላንት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን አራተኛው ፓትርያርክ እያሉ ፎቷቸውን በራሳቸው ላይ አስቀምጠው ሲያከብሯቸው ኖረው አሁን ሥራ ለመሥራት ሲነሡ ሊኮንኗቸው መጀመራቸው ወደው ሳይሆን ተገደው የተሰደዱ ሕጋዊ ፓትርያርክ መሆናቸውን ረስተውት ይሆን? እንግዲያውስ "አላዋቂ የሰማ ዕለት ያብዳል" ነውና የረሱትን አሁን እዚህ እናስታውሳቸው!!

1. **ሥልጣኑ የተያዘበት ሕገ-ወጥ አካል መልሶ ቢያወግዝ ውግዘቱ ሊጸና አይችልም።**

ወያኔ ኢሕአዴግ አዲስ አበባ ሲገባ የቤተ ክርስቲያን አባል ያልነበሩትን አባ ጳውሎስን ለፓትርያርክነት ያጨበት ምክንያት አባ ጳውሎስ ከመጀመሪያውም በምንኩስና ሽፋን በረቀቀ ስልት የፖለቲካ ትግሉን ሲያጧጡፉ የቆዩ የወያኔ ታጋይ ስለነበሩ ነው እንጅ። አባ ጳውሎስ ገና ወያኔ ኢሕአዴግ አዲስ አበባ ሲገባ በሥልጣን ላይ እንደሚያስቀምጣቸው ያውቁ ስለነበረ በነበሩበት በሎስ አንጀለስ ቤተ ክርስቲያን "እስከዛሬ ድረስ በአማርኛ በማገልገል በድያችኋለሁ፤ ከዛሬ ጀምሮ ግን ስብከትም ሆነ ቅዳሴ የሚከናወነው በትግረኛ ነው" የሚልና በአንድነትና በፍቅር አብሮ የኖረውን ሕዝብ የሚከፋፍል ቃል በመናገራቸው ይሕ ንግግር የተግባራቸው መገለጫ ሆኖ እስከ አሁንም ድረስ በዚያ አካባቢ ባሉ ምዕመናን ዘንድ በመጥፎ ጎኑ ሲወሳ ይኖራል።

ከሁሉም በላይ ደግሞ አባ ጳውሎስ በሰሜን አሜሪካ በነበሩበት ጊዜ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከድተው ከአባልነት ራሳቸውን አግልለው መኖራቸው ማንም ሊያስተባብለው የማይችል እውነታ ነው። ራሳቸው አባ ጳውሎስ በሎስ አንጀለስ ከተማ በፍርድ ቤት ፊት ቀርበው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባል አይደለሁም ብለው አረጋግጠው በመናገራቸው ፍርድ ቤቱ እንግዲያውስ በአባልነት የሌለህባትንና የማታውቃትን ቤተ ክርስቲያን ስም መጠቀም አትችልም ብሎ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም ቤተ ክርስቲያን እንዳይመሠርቱ ስለከለከላቸው "Apostolic Church" በሚል ስም የራሳቸው ቤተ ክርስቲያን በመክፈት በፍቅርና በአንድነት ተስማምቶ የሚኖረውን የሎስ አንጀለስ ሕዝብ ከሁለት ከፍለው እርስ በራሱ ሲያፋጁት ኑረዋል። ይህንንም ነሐሴ 19 ቀን 1984 ዓ.ም. በታተመው የጦቢያ መጽሔት ላይ ቃለ መጠይቅ ተርጎላቸው ያለ አንዳች ሐፍረት በቃላቸው አረጋግጠው ተናግረዋል።

ስለዚህ አባ ጳውሎስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የማይወክሉ ሆኖ ሳለ በጉልበት ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን አፍርሰው በሥልጣን ላይ በተቀመጡ ጊዜ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ሥራውን በይፋ በጀመረበት ዕለት መስከረም 20 ቀን 1987 ዓ.ም. በኒዮርክ ከተማ አስቀድመው የተወገዙና ሥልጣናቸው የተያዘ በመሆኑ አሁን የሚያስተላልፉት ውግዘት አሳሪነት የለውም፤ ውግዘቱ ሊጸናም አይችልም። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንድ ፓትርያርክና አንድ ሲኖዶስ እንጅ ሁለት ፓትርያርክና ሁለት ሲኖዶስ ሊኖር አይችልም የምንለውም ከዚህ የተነሳ ነው።

2. **በንጹሐን ደም መፍሰስ ተጠያቂ የሆነ ሕገ ወጥ አካል ሕጋዊውን ሲኖዶስ የማውገዝ ምንም ዓይነት ሥልጣን የለውም፤**

"ደም ምድሪቱን ያረክሳታልና የምትኖሩባትን ምድር አታርክሱአት" (ዘኁ 33፡ 35) የተባለውን አምላካዊ ቃል ተላልፎ በካድሪዎች የሚመራና በደም የተነከረ ሲኖዶስ ሌላውን ለማውገዝ ብቃቱም ኃላፊነቱም የለውም። ሲኖዶስ ተብየው የካድሪዎች ስብስብ የማውገዝ ብቃት ቢኖረው ኖሮ የተበተነውን መንጋ በሚሰበስቡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ላይ አይደለም ድምጹን ማሰማት የነበረበት። የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግ ሲፈርስ፣ የተቀደሰው መንበር በደም ታጥቦ ሲረክስ፣ የንጹሐን ኦርቶዶክሳውያን ደም በከንቱ ሲፈስ ያኔ ወኔ አግኝቶ መናገርና የሚደርሰውን መከራ በጸጋ መቀበል ሐዋርያዊነት ነበር። በረዥሙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የዮዲትንና የግራኝን ዘመን እንደገና የሚያስታውሰን በሃይማኖት ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የክርስቲያኖች ደም በከንቱ የፈሰሰበት የግፍ ዘመን ቢኖር የአባ ጳውሎስ ዘመን ነው። ለምሳሌ መጥቀስ ቢያስፈልግ፡

1. በአባ ጳውሎስ ዘመን በጎንደር ከተማ በአደባባይ ኢየሱስ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆነው ወንጌልን ይማሩ በነበሩ ኦርቶዶሳውያን ላይ ጥይት እንደበረዶ ተርከፍክፎባቸው ብዙዎቹ እንደ እሳት ራት ተቃጥለው አልቀዋል። በዚህ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነኝ ብለው ራሳቸውን የሰየሙት አባ ጳውሎስ ያደረጉትን ስለሚያውቁ አንዲት ቃል አልተናገሩም።
2. በደቡቡ የሀገራችን ክፍል በአሰቦት ገዳም የነበሩ መነኮሳትና ምዕመናን ከእነሕይወታቸው ገደል ውስጥ እየተወረወሩ ሲያልቁ አሁን ቤተ ክርስቲያንን እወክላለሁ የሚለው አካል አንዲት ድምጽ አላሰማም።
3. በአባ ጳውሎስ ምክንያት የእርሳቸውን ሕገ-ወጥ ሹመት በመቃወም አዲስ አበባ በቅዱስ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተፈጠረው ግርግር አያሌ ወጣቶች በፖሊስ ቆመጥ ተደብድበው እስር ቤት ገብተዋል፤ ከእነርሱም አንዷ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪ

በድብደባው ምክንያት ሕይወቷ አልፏል፤ የቀሩትም ብዙ መከራና እንግልት ደርሶባቸዋል።

4. አዲስ አበባ ውስጥ በልደታ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርኩን በተቃወሙ ምእመናን ላይ ፖሊስ በተደጋጋሚ በወሰደው እርምጃ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዲያቆናት ተገድለዋል፤ ብዙ ሕይወት ጠፍቷል፤ ብዙ ወጣቶችም ታፍሰው ታስረዋል። በጎንደር፣ በጂማ፣ በአሰቦት ገዳምና በአዲስ አበባ በየአብያተ ክርስቲያናቱ በግፍ የተገደሉ ሰዎች እስከ አሁንም ድረስ ደማቸው እንደ ጻድቁ አቤልና እንደ ዘካርያስ ደም ይፈላል። የተቀጣጠለውም የነገር እሳት ገና አልበረደም።
5. በጥር ወር 1997 ዓ.ም. አዲስ አበባ ውስጥ በቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ለአባ ጳውሎስ የማመልከቻ ደብዳቤ ያቀረቡ ባሕታዊ በአባ ጳውሎስ ጠባቂ ከቤተ ክርስቲያን ዓውደ ምህረት ላይ በጥይት ተደብድበው ተገድለዋል። እንዳይቀበሩና እንዳይፈቱም በየአብያተ ክርስቲያናቱ ትዕዛዝ ተላልፎ የግፍ ግፍ ተፈጽሞባቸዋል።
6. የመንግሥትን አፋኝ ፖሊሲና አምባገነናዊ አገዛዝ የተቃወሙ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከፖሊስ በኩል ሊደርስባቸው የሚችለውን ድብደባ ፈርተው በመንበረ ፓትርያርክ ግቢ በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቢጠለሉ አባ ጳውሎስ ይህን ወንበዴ ሁሉ አስወጣልኝ ብለው አሳልፈው በመስጠት በፖሊስ ቆመጥ እንዲደበደቡና ብዙ መከራና እንግልት እንዲደርስባቸው አድርገዋል።
7. በጥር ወር 1998 ዓ.ም. በጥምቀት በዓል ላይ ሕዝቡ የአባ ጳውሎን ፖለቲካዊ አቋም በመቃወሙ አያሌ ወጣቶች በፖሊስ ቆመጥ እየተደበደቡ ታፍሰው ወደ እስር ቤት ተወስደዋል፤ መከራና እንግልትም ደርሶባቸዋል። ታቦት የተሸከሙ ካህናት ቁጭ በል ተነስ እየተባሉ ተሰቃይተዋል፤ የተከበረው የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓትም በአባ ጳውሎስ ምክንያት ተዋርዷል።
8. አሁን በሥልጣን ላይ ያለው የወያኔ ኢሀደግ መንግሥት ምርጫ ተጭበርብሯል በሚል ሰልፍ የወጡ ወጣቶችን በጥይት ተደብድበው እንዲገደሉ ባደረገ ጊዜ አባ ጳውሎስ ድርጊቱን መቃወም ካለመፈለጋቸውም በላይ ለሞቱት ሰዎች በየአብያተ ክርስቲያናቱ ጸሎተ ፍትሐት እንዳይደረግ በማገድ የፖለቲካ አመራር ሰጭ መሆናቸውን በይፋ አረጋግጠዋል።
9. የአባ ጳውሎስ ፍርፋሪ ይቅርብን የሚመጣብንን መከራ እንቀበላለን በሚል የሕሊና ውሳኔ ወስነው በጥይት ለተደበደቡ ወጣቶች ድምጻቸውን ያሰሙ የቅድሥት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ደቀ መዛሙርት በመመረቂያቸው ጊዜ ከትምህርት ቤት ተባርረዋል።

እንግዲህ በአጠቃላይ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች የማይቆም፣ በኢትዮጵያ ለፈሰሰው የንጹሐን ደም ተጠያቂ የሆነ የካድሬዎች ስብስብ በሕግ አፍራሽነቱ ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያኒቱና በምዕመናን ላይ እየደረሰ ባለው አሳዛኝ ነገር ሊያፍር ሲገባው በስደት የሚገኙቱን ብፁዓን አባቶች ለማውገዝ መሞከር ስንፍና ነው። “የሞኝ ልቅሶ መልሶ መላልሶ” እንዲሉ ይህ ሕገ-ወጥ አካል በተደጋጋሚ ዘጠና ዘጠኝ የውግዘት ቃል ቢደርትም ከላይ እንደተጠቀሰው በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ሥልጣኑ አስቀድሞ የተሻረ በመሆኑ ግዝቱ ሊጸና የማይችል ከንቱ ግዝት ወይም ወፈ ገዝት ይባላል።

ስለዚህ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ከቅዱሳን አባቶች ጀምሮ በተዋረድ በመጣው ሕጋዊ ሥልጣኑ ጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. የአራት ኪሎው ሕገ-ወጥ ሲኖዶስ ያስተላለፈውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል። በተቃራኒው ደግሞ በአባ ጳውሎስና በጭፍሮቻቸው ላይ ለሁለተኛ ጊዜ የሚከተለውን የውግዘት ቃል አስተላልፏል።

# ቃለ ውግዘት

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ጾሙ፥ በፍቅረ ሢመት ለመፈታተን ወድቀህ ሰገድልኝ በማለት በድፍረት የቀረበውን ፈታኝ፣ «ሑር እምድኅሬየ ሰይጣን»ብሎ እንደ ገሰጸው፤ (ማቴ 4፥10)።

ዳግመኛም በቅዱስ ጴጥሮስ አድሮ፥ ያዘነ መስሎ፥ «ጌታ ሆይ ይህ ከቶ አይደርስብህም »ብሎ፥ ምሥጢረ ሞቱን ለማስተባበል የሞከረውን ፈታኝ፤ «ሑር እምድኅሬየ ሰይጣን» «ሰይጣን ! ከኋላየ ሂድ፤ እንቅፋት ሁነህብኛልና፥ የሰውን እንጅ፥ የእግዚአብሔርን አታስብምና» ብሎ እንደገሰጸው (ማቴ 16፥23)።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው በስደት ሀገር የሚገኘው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ፥ እንደ ለመደው ጾሙን ተጠግቶ የቤተ ክርስቲያናችንን ሰላማዊ ጉዞ የሚያደነቃቅፈውን በአባ ጳውሎስ የሚመራውን ሕገ ወጥ የወያኔ ሲኖዶስ «ሑር እምድኅሬየ ሰይጣን» «ሰይጣን ! ከኋላየ ሂድ፤ እንቅፋት ሁነህብኛልና፥ የሰውን (የወያኔን) እንጅ፥ የእግዚአብሔርን አታስብምና» በማለት። በቤተ ክርስቲያን ራስ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን፣ በቅዱሳን አባቶቻችን በሐዋርያትም ሥልጣን፥ «ወጉዝ ከመ አርዮስ» በማለት አውግዟቸዋል።

1. አባ ጳውሎስም ከዛሬ ጀምሮ፥ ሥልጣነ ክህነታቸውና ጳውሎስ የሚለው የማዕርግ ስማቸው በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የተገፈፈና የተሻረ ስለሆነ፤ ይህ ቃለ ውግዘት ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ አባ ገብረ መድኅን ገብረ ዮሐንስ ተብለው እንዲጠሩ ወስኖባቸዋል። በሕይወትም ሆነ በሞት፥ ምንም ዓይነት መንፈሳዊ አገልግሎት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንዳይፈጸምላቸው ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዞ ከቤተ ክርስቲያን ለይቷቸዋል።
   ዝክረ ስማቸውም፥ ከኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪካዊ ጠላቶች ጋር እንዲቆጠር በጽኑ ውግዘት ወስኖባቸዋል።

2. አባ ገብረ መድኅን ገብረ ዮሐንስን በሕገ ወጥነት በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ አድርገው የሾሙት ጳጳሳትም ከዲቁና እስከ ጵጵስና ያለው ሥልጣናቸው የተሻረና የተገፈፈ ስለሆነ፣ በሕይወትም ሆነ በሞት፥ ምንም ዓይነት መንፈሳዊ አገልግሎት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንዳይፈጸምላቸው ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዞ ከቤተ ክርስቲያን ለይቶአቸዋል።

3. በአባ ገብረ መድኅን ገብረ ዮሐንስ እጅ የተሾሙት ጳጳሳትም ከዲቁና እስከ ቅስና ያለው መንፈሳዊ ሥልጣናቸው የተገፈፈ ስለሆነ፥ በኢትዮጵያ ኦርቶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምንም ዓይነት መንፈሳዊ አገልግሎት እንዳይሰጡ ቅዱስ ሲኖዶስ ከቤተ ክርስቲያን አንድነት አውግዞ ለይቷቸዋል

# ማጠቃለያ መልእክት፤

የተወደዳችሁ በሀገር ውስጥ በገዳማትና በአድባራት የምትገኙ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያ ንና በዓለም ዙሪያ የምትገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን በሙሉ፤

እንደሚታወቀው ሁሉ ሀገራችን ኢትዮጵያ በዘረኛው የወያኔ መንግሥት ግፈኛ አስተዳደ ር፣ ቤተ ክርስቲያናችንም ወያኔ ለክፋቱ ይበጀኛል ብሎ ባቋቋመው ሕገ ወጥ ሲኖዶስ፥ እየተፈጸመባት ያለው ግፍና በደል ከቀን ወደ ቀናት፣ ከዕለት ወደ ዕለታት፣ ከዓመት ወደ ዓመታት፥ እየጨመረና እየባሰ ይኸውና አስራ አምስት ዓመት ሆነ።

ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፥ «እኔ በሥጋየ ከእናንተ ጋር ባልኖር፥ በመንፈሴ ከ እናንተ ጋር አለሁ፤ እነሆ ከእናንተ ጋር እንዳለሁ ሁኘ፥ ይህን ሥራ የሠራውን እፈርድ በታለሁ፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተሰብስባችሁ በእኔ ሥልጣን፥ በጌታችን በ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ለሰይጣን አሳልፋችሁ ስጡት" ብሎ እንደተናገረ (1ኛ ቆሮ 5፥ 3)።

በሀገር ርቀት ምክንያት እናንተ ከእኛ ጋር እኛም ከእናንተ ጋር በአካለ ሥጋ አንድ ላ ይ ባንሆንም፥ በመንፈስ፥ በዓላማና፥ በአቋም፥ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓት ርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከሚመራው ከሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጋር ሁናችሁ፥ በሕገ ወጡ በአባ ገብረ መድኅን በሚመራው የወያኔ ሲኖዶስ ላይ ያስተላለፍነውን ቃለ ውግዘት እንድታከብሩ፣ አባ ጳውሎስንም አባ ገብረ መድኅን ብላችሁ እንድትጠሩ፣ በጌታችን፣ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛችሁአለን "ደም አፍሳሹንና ሸንጋዩን ሰው እግዚአብሔር ይጸየፋል" ተብሏልና (መዝ 5፡6)።

በተጨማሪም በሕገ ወጡ ፓትርያርክ በአባ ገብረ መድኅን በሚመራው ሕገ ወጥ ሲኖዶስ ስም የተላለፈ የሀሰት ውሳኔና ውግዘት ሁሉ በዚህ ውሳኔ የተሻረና የተደመሰሰ መሆኑን እናስታውቃለን። በሕጋዊው ሲኖዶስ የተወገዙትን የአባ ገብረ መድኅንና የመሰሎቻቸውን ቃል እንዳትሰሙ፣ ትምህርታቸውን እንዳትቀበሉ፣ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ከእነርሱ ጋር ኅብረት እንዳይኖራችሁ፤ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው በስደት ሀገር የሚገኘው ሕጋዊ ው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዞአል።

መዋዕለ ጾሙን የድል ጾም ያድርግልን።

እግዚአብሔር አምላክ በሀገራችን በኢትዮጵያና በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያ ናችን መልካም እና ሰላማዊ አስተዳደር ሰፍኖ የምናይበትን ጊዜ ያሳየን።

ሰላም ለሀገራቸን ለኢትዮጵያ ይሁን፤
ሰላም ላለንባት ሀገር ለአሜሪካ፤
ሰላም ለመላው ዓለም ይሁን። አሜን።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው በስደት ሀገር የሚገኘው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክር ስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ፤

ጥር ፴ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. ዋሽንግተን ዲሲ